ነሐሴ 27 ቀን 2010ዓም

ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቂ
ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ ( ፋኖ )
እና
ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት:

ከሁሉ አስቀድመን ወገናዊ ሰላምታችንን እናቀርባለን፡ በመቀጠል አብን በማድረግ ላይ ያለውን ሀገርና ወገን አድን ትንቅንቅ በታልቅ አክብሮት እያወደስን ከጎኑ ቆመን አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነን። የኢሕብፓና የኦሕንኢአ አባሎች በጋራ ተሰብስበን የአብን የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅድ በመገመግም በጋራ መሥራት ይቻላል ብለን ድምዳሜ ላይ ደርሰናል:: በየክፍለ ሀገራቱ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ መብታቸው እንዲጠበቅ ማድረጉ በጣም የሚያስደስት ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ ጅምር አያቶቻችን ሲጠቀሙበት የኖሩ ስልት ነው። ዛሬም ለአንድነታችን ትልቁ መሠረት ሆኖ አግኝተነዋል። የዛሬው ተደመሩ ትጥቃችሁን ፈትታችሁ ጀሌ ሁኑ ማለት ለተደማሪው ፓለቲከኛ እና ተቃዋሚዎች ባዶ መፈክር ነው:: የተደማሪዎች ግርግር ደግሞ ሕዝባችን የጠየቀውን መሠረታዊ ለውጥ ወደ ጎን በማድረግ ለጥገናዊ ለውጥ መንበርከክ ማለት ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የታገለው ራሱ የሚመርጠዉን እንጂ ኢሕአድግ የሰየመለትን ሥዩም ዴሞክራሲን ለማፅደቅ አይደለም:: በመደመሩ መፈክር መጃጃልም ለተገጣይ እና አሥገንጣይ ግዜ መግዣ ነው እንጂ ለብሄራዊ አንድነታችን ጠቀሜታ የለውም አና ከሕዝብ አካል ከሆኑት አብን እና መሠል ድርጅቶች ጋር አብሮ መሥራት ግዜው የግድ ይላል:: በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ ና የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጺያ አንድነት ከአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ጋር አብሮ ለመሥራት ጥሪውን ያቀርባል::

| | |
|---|---|
| ኢሕብፓ EPNP የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY | ኦሕንኢአ OPMEU |

EPNP.INFO

ኢሕብፓ

EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY